ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሣን*

ቅጽ 50፣ ቁ.1 ሚያዝያ፣ ፪ ሺህ ፲፬ ዓ. ም

# አገራችን ዛሬም አደጋ ላይ ነች!

*የሥነ ምድር ጥናቶች እንደሚያሳዩት ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ (ሉሲ)፣ የሦስት ሚሊዮን ዘመን ባለፀጋ የሆነች ምድር ነች። ኢትዮጵያ የታላቁ የዜማ ሰው የቅዱስ ያሬድም አገር ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 43 ጊዜ ሰሟ የተጠቀሰ ሲሆን የመጀመሪያው ጥቅስ ኦሪት ዘፍጥረት 2:13 "የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል" ይላል። "ትንቢተ-ኤርሚያስም በ13:23 "በእውን ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁን"? ይላል። በእስልምና ዕምነት የታሪክ ማኅደር ውስጥም የመጀመሪያውን ፍልሰት "የስደተኛ መዳረሻ ገነት" የሚል ስያሜ ያሰጣት ወይም ሂጅራን ያስተናገደችው ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ መሆኗን ያወሳል።*

*ታላላቅ የዓለም ዕምነቶች ወደ ተለያዩ አገራት ከተስፋፉበት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ከማንኛውም አገር አማንያን በላይ ቅዱሳን መጻሕፍትን በትክክል ተከታዮች መሆናቸውን የአሜሪካ የጥናት ማዕከል (ፒው ሪሰርች) እንደ ምሳሌ ይገልጻል። ዓለም ለምትገዛበት የሞራል ሕግጋት ከማንም አገር አማንያን በላይ የሞራል ባለቤቶች ነን።*

*ኢትዮጵያ የታላቁ የግዮን ወንዝ መነሻ ናት፡፡ በዓለም ውስጥ ከሚገኙት ወንዞች ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚፈሰው ረጅሙ ወንዝ ኢትዮጵያዊው የአባይ ወንዝ ነው፡፡ አባይ ከኢትዮጵያ ተነስቶ የተጠሙ አናፍስትን ጥማት እያረካ 6,650 ኪሎሜትር (4,130 ማይል) ተጉዞ የሜዲትራኒያንን ባሕር ከመቀላቀሉ በፊት ለግብፃውያን የዕለት ጉርስና የኤሌትሪክ መብራት ለጋሽ የሆነው ወንዝ ምንጭ የሆነች የተፈጥሮ ፀጋ ባለሀብት አገር ኢትዮጵያ ነች።*

*ኢትዮጵያ የውጭ ወራሪዎችን መክታ ፀንታ የኖረች አገር፣ ሕዝቧም በነፃነቱ ሳይደራደር መስዋዕትነት እየከፈለ እስከአሁኑ ዘመን ላይ ደርሰናል። ከዘመነ-ሥልጣኔ ጀምሮ አገራት የድንበር ማስፋፋት ጦርነቶች ሲቀሰቅሱና ሌሎችን ለመንጠቅ ሲዋጉ፣ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ያልሰጡ የሌሎችንም አክብረው የኖሩ ናቸው። ኢትዮጵያ ስለሌሎች አገራት የነፃነት ተጋድሎ ደማቅ ሰንደቅ የሆነች እንጂ የአገራትን በነፃነት የመኖር መብትን ተጋፍታ የማታውቅ አገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ የነፃነት ቀንዲል በመሆኗ በጥቁር ሕዝቦች ዘንድ ታላቅ ቦታ የተሰጣት አኩሪ አገር ስትሆን ምዕራባውያን ግን ለኢትዮጵያን ክብርም ሞገስም*

ሰጥተዋት አያውቁም፣ ሊሰጧትም አይችሉም፣ ከመሠረታዊ ጥቅማቸው ጋር ይጋጫልና። ከቅርብ የድንበር ተጋፊ ጎረቤቶች እስከ የሩቅ ወራሪዎች በኢትዮጵያ ላይ አያሌ ጦርነቶችን ሲከፍቱባት ኖረዋል፡፡ ባዕዳን ባህር አቋርጠው ለወረራ የመጡትንም ሆነ የጉርብትና ኬላ ሰብረው ለመስፋፋት የሞከሩ ጠላቶቻችንን ኢትዮጵያ አሳፍራ መልሳቸዋለች፡፡ ኢትዮጵያውያን ሰው አክባሪና እንግዳ ተቀባዮች መሆናቸውን ዓለም የመሰከረልን፣ የሃይማኖት ድርሳናት ያሞገሱን ነን፡፡

ኢትዮጵያ የዓለም ታላላቅ ሃይማኖቶችን፣ እስልምናን፣ ክርስትናን፣ አይሁድነትና ሌሎች ዕምነቶችን ጭምር የተቀበለችና ያስተናገደች፣ የየሃይማኖቶቹ ተከታዮችም ተከባብረው የኖሩባት ቅድስት ምድር ነች፡፡ ከግራኝ መሐመድ መነሳትና ከዚያም በኋላ የጎረቤት ሀገራት (ግብፅ፣ ሶማሊያና ሱዳን) ለሌሎች ባህር አቋርጠው ድንበር ሰብረው ለመጡ የአገራችን ጠላቶች አጋዥና ተባባሪ በመሆን ኢትዮጵያን ወርረው አስወርረዋል፡፡ የመካከለኛው ዘመን ኃያል የነበረችው ኦቶማን ቱርክ ለግራኝ መሐመድ መነሳትም ሆነ ከዚያ በኋላ ለተደረጉ ድንበር ተሻጋሪ ጦርነቶች ዋና ተዋናይ በመሆን ደጋግማ ወግታናለች።

ግብፅ በሰሜንና በምሥራቅ ተደጋጋሚ ወረራ አካሂዳ በጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች ክንድ ድባቅ ተመትታ የተመለሰች ቢሆንም በሱዳን ታዝላ የእጅ አዙር ጦርነት ፈጽማብናለች፣ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ ነው፡፡ የደርቡሽ ወረራ እየተባለ የሚጠራው ሱዳን ድንበር ጥሳ እስከማህል አገር ወረራ አድርጋ፣ ለግብፅ በማገዝ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሱዳን እራሷ ባላት የግዛት ማስፋፋት ፍላጎት ተደጋጋሚ ሙከራ አድርጋለች። ግብፅና ሱዳን የኢትዮጵያን ግዛት ለመያዝ ወረራ ሲፈጽሙ ምዕራባውያን ምንጊዜም ከጀርባ ነበሩ፣ አሁንምን አሉ፡፡ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ እስከ 1900 ዓ. ም ድረስ የተካሄዱ ጦርነቶች ሁሉ ድንበር ዘለልና የአገራችንን ሉዓላዊ ግዛት የደፈሩ፣ በጉልበት መሬትን ለመቀማት፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሕዝቧን በቅኝ ግዛት ሥር ለማድረግ የተካሄዱ ጦርነቶች ነበሩ። በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ እናቶች ልጆች ወልደውና አሳድገው ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ለማብቃት ያልታደሉ የወላድ መካኖች እጅግ ብዙ ነበሩ፡፡ ያኔም እንደዛሬው ልጆቻቸውን በጠላት የተነጠቁ የኢትዮጵያ እናቶች የዕድሜ ዘመን ዕንባ አንብተው አልፈዋል።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን ድንበር ጥሶ ከመጣ የውጭ ጠላት ጋር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ላይ ከጣሊያን ቅኝ ገዥ ጋር የተደረገው የመከላከል ጦርነት አምስት ዓመት ያስቆጠረና የሺዎች ዜጎችን መስዋዕትነትን ያስከፈለ ነበር፡፡ ከፍተኛ የሕዝብ ሕይወት የተገበረበት ቢሆንም አገርን እንደ አገር ማስቀጠል ግን ተችሏል። ሕዝባችን ከአንድ የውጊያና ዘመቻ ሳያገግም ወደ ሌላው ዘመቻ፣ ወደ ሌላ ጦርነትና ሰማዕትነት ሲሸጋገር ኖሯል። ጦርነቶቹ ሁሉ ወደንና ፈልገን የገባንባቸው ሳይሆኑ ተገደን የአገራችን ክብር አናስነካም ብለን ያካሄድናቸው የጎልውና ጦርነቶች ነበሩ፡፡

በዓለም የፖለቲካና የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ውስጥ አገራት ቋሚ ጠላት ወይንም ቋሚ ወዳጅ የላቸውም ይባላል፡፡ ወዳጅነትና ጠላትነት የሚለካው በጥቅም ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ጠላቶች ግን ለዘመናት ተለውጠው የማያውቁ መሆናቸውን ታዝበናል። በታሪካችን ከሁለትና ሦስት መቶ ዓመታት በፊት የወጉን አገራት ዛሬም

ከጀርባችን አልወረዱም። ዛሬም ጊዜ ጠብቀው የሚያጠቁን እነዚያው የጥንቶቹ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ናቸው።

የኢትዮጵያ እናቶች ጀግና ወላዶች ቢሆኑም እንባቸው እንደጅረት ሲፈስ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ የትናንት እናት ገመድ ታጥቃ በከፍተኛ ሃዘን እንዳለፈችው ሁሉ ዛሬም የታሪክ አዙሪት ይመስል ያለጧሪና ቀባሪ የሚያልፉት ወላጆች ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ የእንባው መንሥኤ የውጭ ጠላቶቻችን የፈጠሩት ብቻ አይደለም። ከዮዲት ጉዲት ጊዜ ጀምሮ፣ ግራኝ መሐመድ ጨምሮ እስከ ዘመነ ህወሓት ድረስ የተዘመተው ከውስጥ በሚነሱ አገር-በቀል ጠላቶች ነው። እነዚህ ጠላቶች መልካቸው፣ ቋንቋቸውና የቆዳ ቀለማቸው ኢትዮጵያውያን ያሰኛቸው እንደሆነ እንጂ ነገረ-ሥራቸው አገርን የማፍረስና የማጥፋት እኩይ ዓላማ ነው።

አገራችንና ሕዝባችን የተፈጥሮ ሃብታቸውን እንዳይጠቀሙ በየዘመኑ በተነሱብን ጠላቶቻችን ታግዶ ልጆቿ ለውጭ እርጥባን ተዳርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ ቋሚ ጠላት ተሸክማ ከዘመን ዘመን እየተሻገረች እዚህ የደረሰችው ዜጎቿ ለዕድገቷ፣ ለብልጽግናዋ፣ ለሥልጣኔ ግስጋሴዋና ለሁሉም ዜጋ የኑሮ መሻሻል ከመሥራት ይልቅ የአገሪቱን ሉዓላዊ የግዛት አንድነትና የሕዝቧን በነፃነት መኖር ለማስቻል ድንበር በመጠበቅና ከወራሪ ጋር በመታገል ነው። በየዘመኑም ደምና ዕንባ ሳያቋርጥ እንደጎረፈ እነሆ የአሁኑ ዘመን ላይ ደርሰናል። የውጭ ጠላቶቻችን ይህን ሁሉ ዘመን ኢትዮጵያን ለማዳከም ሲሞክሩ ሙከራቸውን ለማሳካት የውስጥ ቅጥረኛ ከሃዲም አጥተው አያውቁም፡፡

ኢትዮጵያ ነፃነቷን በደም ፍሳሽና በአጥንት ክስካሽ እንደጠበቀች ሁሉ ጥቁር ሕዝቦችን ከባርነትና ከአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣትና አፍሪካውያን እንደ ሌሎቹ አህጉራት ሕዝቦች በነፃነት እንዲኖሩ ትልቁ ተጋድሎ የተደረገው በኢትዮጵያ ሕዝብ መሪነት ነበር። ኢትዮጵያ ከጣሊያን ወረራ ማግሥት ጥቅምት 14 ቀን 1937 ዓ. ም ሳንፍራንሲስኮ ኮንቬንሽን ላይ ተካፋይ በመሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲመሠረት ከመሥራች አገሮች አንዷ ነበረች፡፡ ከቱኒዝ እስከ ኬፕ ታውን፣ ከሞቃዲሾ እስከ ዳካር በተደረጉት የነፃነት ተጋድሎዎች የኢትዮጵያ የድጋፍ አሻራ ያላረፈበት የነፃነት ትግል የለም፡፡ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1966 ዓ. ም የደቡብ አፍሪካን የአፓርታይድ ሥርዓት በአመፅ ለመለወጥ በተደረገው ትግል የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ መሪዎችን በማሠልጠንና የመሣሪያ ድጋፍ በመስጠት የኢትዮጵያ ተሳትፎ የጎላ ነበር። በቀጣይ ዓመታትም በዛኑና በዛፑ የተመራውን የሮዴሽያ የነፃነት ትግል ኢትዮጵያ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ሮዴሺያ (የአሁኗ ዚምባቡዌ)ን ነፃነት አስረግጣለች። በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ፣ አንጎላ፣ በመካከለኛው አፍሪካ፣ በምሥራቅና በምዕራብ አፍሪካ በተደረጉ የነፃነት ተጋድሎዎች ሁሉ የኢትዮጵያ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነበር።

ግንቦት 25 1963 ዓ. ም (እአአ) የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ32 ነፃ አገራት ሲመሠረት፣ አረቦች በግብፆች አማካኝነት ድርጅቱ እንዳይቋቋም ከፍተኛ ጫና ቢያደርጉም ኢትዮጵያ ከጋናው መሪ ከክዋሚ ኒክሩማና ከሌሎች መሪዎች ጋር በመሆን ጠንካራ ትግል በማድረግ ድርጅቱን እውን ልታስደርገው ችላለች፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታውን በአዲስ አበባ ያደረገው ስብሰባ በቀጣይ ዓመታት የድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤትም አዲስ አበባ እንዲሆን

ወሰነ። ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተመሠረተ በኋላ ከ20 ያላነሱ በቅኝ ግዛት ሥር የቆዩ አገራት ለነፃነታቸው ያደረጉትን ትግል ለማገዝ ችሏል፡፡

ኢትዮጵያ የአህጉራችንንና የዓለምን ሰላም ለማስከበር ለረጅም ዓመታት ተሳትፋለች፡፡ ይሁን እንጂ አመድ አፋሽ እጆች እንደሚባለው ኃያላኑ መንግሥታት ጥንትም ሆነ ዛሬ ለአገራችንና ለሕዝቧ መልካም ምላሽ ሳይሆን ጨርሶ እንድትጠፋ ፖሊሲ ቀርፀው በመውጋትና በማስወጋት እዚህ ዘመን ላይ ደርሰናል።

ከየካቲት 1966 ዓ. ም አብዮት ማግሥት የተከተለው የአገራችን ሕዝብ መከራና ፍዳ ለዘመናት ከነበሩትና ከታዩት ሁሉ የከፋ ነበር። የወታደሩን ወደ ሥልጣን መውጣት ተከትሎ ለእኩልነት፣ ለመሬት ላራሹ፣ ለዴሞክራሲ የታገሉ አብዮታውያን ሕዝባዊ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ጥያቄዎቹን ደግመው በማንሳታቸው ምላሹ የጅምላ ግድያ መሆኑ አገራችን አሁን ለደረሰችበት ከፍተና ቀውስ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ በየአቅጣጫው ለተነሱ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ጥያቄዎቹ በወታደራዊው አፋኝ አገዛዝ እንዲመክኑ ሆኑ፡፡ በዚህ ወቅት ነበር ጠባብ ብሄርተኞች በየአካባቢው ያቆጠቆጡትና ኢትዮጵያን ለመበተን ሤራ የጀመሩት፡፡ ወታደራዊው መንግሥት የሕዝባዊ መንግሥትና የዴሞክራሲን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ በነፃ እርምጃና በቀይ ሽብር ወደ ጭፍጨፋ በመግባቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን ለሞትና ለስደት ተዳርገዋል።

በ1969 ዓ. ም በኢትዮጵያ ውስጥ የቀይ ሽብር ፍጅት በነገሠበትና ጥቁር ዳመና ባጠላበት ወቅት በአሜሪካ ተደገፋ ሶማሊያ በአገራችን ላይ ወረራ ፈጽማለች። በዚያን ወቅት በውጭና በውስጥ የሕዝብና የአገር ጠላቶች ጥቃት ኢትዮጵያን በከፋ ጊዜ ውስጥ እንድታልፍና ልጆቿን እንድትገብር ሆናለች፡፡ ለ17 ዓመታት የቀጠለው የወታደራዊው አምባገነን አገዛዝ መሪው አገር ጥሎ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ አገራችንን በጦርነት አዙሪት ውስጥ በመዝፈቅ ዜጎቿን ለሞትና ለስደት በመዳረጉ በውጭ ኃይላት የተደገፉ ጠባብ ብሄርተኞች አገርን በቀላሉ እንዲቆጣጠሩና በትረ-መንግሥቱን እንዲጨብጡ አድርጓል፡፡ የውጭና የውስጥ ጠላቶች "ጊዜው የእኛ ነው" በሚያስብል አኳኋን ህወሓት ዜጋን በዘር የከፋፈለ ልዩ የሆነ የፌደራል አወቃቀር ፈጥሮ ኢትዮጵያዊነት እንዲከስም፣ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ በጠላትነት እንዲተያይ በማድረግ በነፍጥ ኃይል ለ27 ዓመታት ሕዝቡን ረግጦና አፍኖ ሲገዛ ኖረ፡፡ አማራ ዋነኛው ጠላት ነው በማለት ለትግራይ ወጣቶችም በስፋት አስተማረ፡፡ ሤረኛና ዘረኛው የህወሓት ቡድን በሕዝባዊ ትግል ከወደቀ በኋላ በታሪካዊ ጠላቶቻችን ታግዞ ቢችል ወደ ሥልጣን ለመመለስ ካልተሳካ ደግሞ አገራችን ለማፈራረስ አሁንም ሕዝብ እያሸበረና እየገደለ ይገኛል፡፡ የህወሓት ዘረኛ ቡድን አዲስ አበባን ለቆ ቢሄድም አገራችንን በዘርና በቋንቋ ሸንሽኖ ያዋቀረው የአገዛዝ ሥርዓት ግን በአገራችን ውስጥ እንዲቀጥል በመደረጉ አሁንም ለብዙ ሺዎች ሞትና በሚሊዮኖች ለሚቆጥሩ መፈናቀሎች ዋና ምክንያት ሆኖ ቀጥሏል።

ዛሬ እየተካሄደ ያለው ጦርነት በአማራና በአፋር ሕዝብ ላይ ያስከተለው የሕይወትና ንብረት ጥፋት መጠነ-ሰፊ ከመሆኑም በላይ አገሪቱ የገነባቻቸውን መሠረተ ልማቶችና ኢንዱስትሪዎችን አውድሟል። የህወሓት አመራር በሕዝብ አመፅ ከሥልጣን ከተወገደ በኋላ ለሦስት ዓመታት መቀሌ ውስጥ መሽጎ እራሱን ሲያደራጅ ከቆየ በኋላ ከ20 ዓመታት በላይ

ሰላም ሲያስከብርና የሕዝብን ደህንነት ሲጠብቅ የኖረውን የሰሜን ዕዝን በተኛበት ጨፈጨፈ። አገር በመክዳት ተወልዶ በክህደት ያደገው ህወሓት በሥራዊቱ ላይ የጭካኔ እርምጃ ለመውሰድ ያደፋፈረው 30 ዓመት ሙሉ ትግራይ ውስጥ የቀበረውን መሣሪያና ገንዘብ ተማምኖና በፀረ-ኢትዮጵያ የውጭ ኃይሎች አይዞህ በመባሉ ነው፡፡ የህወሓት የአመራር አባላት በተለያየ አጋጣሚ እኛ ኢትዮጵያን ካልገዛናት ትፈርሳለች፣ ለማፍረስም እስከ ገሃነም ድረስ እንሄዳለን ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

ህወሓት እያካሄደ ያለው መጠነ-ሰፊ ወረራ በድንገት የተጀመረ ወይም የአሸባሪው ቡድን መሪ እንዳለው "የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግሥታት ተባብረው ሊመቱን ሲሉ ቀደምናቸው" እንደሚለው እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ የሚያውቀው ነው፡፡ ለምን ቢባል የህወሓት አመራር ለ44 ዓመታት የተዘጋጀበትና ሌላውን አዳክሞ ታላቋን ትግራይ ለመመሥረትና በአፍሪካ ቀንድ ኃያልና የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ በማለምና ተወዳዳሪ እንዳይኖራት ኢትዮጵያን እንደ ዩጎዝላቪያ ትንንሽ ሪፐብሊኮች የማድረግ ዋና ዓላማው ስለነበረ ነው። ይህንን እኩይ ዓላማውን እውን ለማድረግ የህወሓት አመራር እያካሄደው ያለው ወረራና ሽብር በሰላማዊ ዜጎች ላይ ያስከተለው የሞትና የስደት ጥፋት በአገራችን ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ወንጀል ነው።

በዚህ የማን አለብኝና የውክልና ጦርነት ምዕራባውያን የራሳቸውን አሻንጉሊት መንግሥት በአገራችን ላይ ለመትከል ስለሚፈልጉ ህወሓትን ከመቃብር አፋፍ አንስተው አሁን እየፈጸመ ያለውን ወረራ በሙሉ ልባቸው እንደሚደግፉ ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ዕድገትና ብልጽግና ተስፋፍቶ፣ ዜጎች ኑሯቸውን ለማሻሻልና የአገሪቱን ምርት በማሳደግና ገበያን ማስፋፋት እንዳይቻል ምዕራባውያን አገራችን ውስጥ የማያቋርጥ ጦርነት እንዲሰፍን አድርገዋል፡፡ ለምን ይሆን ምዕራባውያን ዓይናቸውን አገራችን ላይ የጣሉባት? ይህ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም የኢትዮጵያ የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በምዕራባውያን የንግድ መንገድ በር ላይ በመሆኑ፣ የነፃነት ተምሳሊት፣ የአባይ ባለቤት፣ ለዘመናት የበለጸገ ታሪክ ያላት አገር በመሆኗና በአገራችን ውስጥ የልዩ ልዩ ማዕድናት መኖር የምዕራባውያንን ኢንዱስትሪ የሚያኳኳ በመሆኑ ነው ከአሜሪካ እስከ አውሮፓ፣ ከተባበሩት መንግሥታት እስከ ግብፅና ሱዳን ከፍተኛ የማጥቃት ርብርብ የሚያደርጉብን ብለን እናምናለን፡፡

አሜሪካ ኢትዮጵያን ለምን ጠምዳ ያዘች ለሚለው ጥያቄ ፤በኢሕአፓ ዕይታ ጠቅለል ባለ መንገድ ለመግለጽ የቀይ ባሕር በር ጉዳይ፣ የአባይ ጉዳይ፣ ኢትዮጵያ ዘመን ተሻጋሪና አኩሪ ታሪክ ያላት ሌሎችን የአፍሪቃ አገሮችን የምታሰባስብ፣ በምሥራቅ አፍሪቃ አገሮች ተሰሚነት ያላት በመሆኑ እንዲሁም ከቻይና ጋር ያላት የንግድና ዘርፈ-ብዙ ግንኙነቶች ለአሜሪካ እንቅልፍ የሚነሱ በመሆናቸው ነው፡፡ አሜሪካ ህወሓትተመልሶ ሥልጣን ሊይዝ ከማይችልበት ደረጃ መሆኑን ያውቃሉ፣ ፍላጎታቸው ህወሓትን ተጠቅመው ኢትዮጵያ ማዳከም ነው፡፡

ህወሓት በተቆጣጠራቸው የወሎ፣ የጎንደርና የአፋር ከተሞችና ቀበሌዎች ሁሉ የዘር ማጥፋት ወንጀል በመፈጸም ላይ መሆኑን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ ድርጅት ኢሰመጉና

አምንስቲ ዓለም አቀፍ ያቀረቡት ዘጋባ ያረጋግጣል። ህወሓት በጥቅምት ወር 2013 ጦርነቱን ሲጀምር ሳምሪ እየተባለ የሚጠራው የምዕራብ የህወሓት ልዩ ኃይል በወልቃይት ማይካድራ ላይ 600 ንፁሃን ወገኖቻችንን ረሽኖ ወደ ሱዳን መሻገሩ የሚታወቅ ነው። በአፋርና በአማራ ክልሎች እየተካሄደ ባለው የህወሓት ወረራ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ዜጎች መፈናቀላቸው እንዳለ ሆኖ፣ ህወሓት በደረሰባቸው ከተሞች ሁሉ ወጣቶችን እየረሸነ እንደሆነም ይታወቃል፡ ፡ ወረራና የሽብር ተግባሩን በመቀጠል በሰሜን ሸዋ ደግሞ ከሌላው አሸባሪው የኦነግ ሸኔ ቡድን ጋር ጥቃቱን በማቀናበር ግድያና ንብረት ዘረፋ እየፈጸሙ ይገናሉ፡፡

ህወሓት በሥልጣን በቆየባቸው ዓመታት አገር ለማፍረስ የሚተባበሩ ቡድኖችና ድርጅቶችን በመላ አገሪቱ ውስጥ እውን እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ እነዚህ ኃይሎች በአፍራሽ ሚና ተሰማርተው ከፍተኛ ጥፋት እያደረሱ በመሆኑ ፅንፈኞች በቤኒሻንጉል ሰው ያፍናሉ፣ ይገድላሉ ያፈናቅላሉ፣ እናቶችን ይደፍራሉ፡፡ በሌላ በኩል ኦነግ ሸኔ ከሰሜን ሸዋ እስከ አሶሳ፣ ከባሌ እስከ ሞያሌ ከፍተኛ ወንጀል እየፈጸመ ይገኛል፡፡ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ ሰው ይገደላል፣ ከተማ ይዘረፋል፣ ያቃጠላል፡፡ የኦነግ ሸኔ መንቀሳቀሻና የጀርባ ምሽጉ ሱዳን መሆኗም ይታወቃል፡፡

ሱዳን በአገራችን የተፈጠረውን የእርስ በርስ ጦርነት እንደ አጋጣሚ በመጠቀም ድንበራችንን ተሻግራ ጦሯንና ገበሬዎቿን ከማስፈሯም በላይ ወደ ሱዳን የሸሹትን የህወሓት ወታደሮችንና ወጣቶችን እያሰለጠነች በተደጋጋሚ ጦርነት ከፍታለች፡፡ ግብጽና ሱዳን የጋራ ጦር በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር ላይ እያሰለጠኑ መሆኑን የራሳቸው ዘጋቢዎች ሳይቀሩ ገልጸዋል፡፡ የአሜሪካ ልዑካን ካይሮና ካርቱም በመመላለስ ከመሪዎቹ ጋር የሚያደርጉት ምክክር ሽብርተኛው ህወሓት እንዴት እንደሚረዳና ኢትዮጵያን እንዴት እንደሚያዳክሙ የሚደረግ ደባ እንደሆነ ለማንም የሚሰወር አይደለም፡፡

አሜሪካ በተናጠል በአገራችን ላይ እስካሁን ድረስ አነስተኛ ናቸው ያለችውን ማዓቀብ ከመጣሏ በተጨማሪ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እንደምታደርግ በማስፈራራት በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ጫና ለመፍጠር እየጣረች ነው፡፡ ሌሎች አገሮችም፣ የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ፣ እንዲተባበሯት እንቅልፍ አጥታ እየሠራች ነው፡፡ ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል እንዲሉ እራሷ ከጀርባ ሆና ለሽብርተኛው ህወሓትና ለግብጾች አማካሪ በመሆን ጦርነቱን እያጦዘች በሌላ በኩል ደግሞ ተኩስ አቁሙ፣ ተደራደሩ እያለች ዓይኗን በጨው ታጥባ ትናገራለች፡፡ ይህ የአሜሪካ ባህሪ ቀደም ብሎም በቬትናም፣ በካምፖዲያ፣ በችሊ፣ በተለያዩ የደቡብ አሜሪካ አገሮች፣ በኢራቅ፣ በፍጋኒስታን፣ በሊቢያ፣ በየመንና በሶሪያ የታየ በመሆኑ "ማንም ሊጠይቀኝ አይችልም" በማለት የፈፀመችው በደል ትልቅ ትምህርት ሊሆን ይገባል፡፡

በኢሕአፓ ዕይታ ጦርነት ጥሩ ነገር ባይኖረውም፣ ይህ ጦርነት ያለጥርጥር ፍንትው አድርጎ ያሳየው ሃቅ ቢኖር የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት እጅግ ጎልተውና ጠንክረው እንዲወጡ ማድረጉ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥና በውጭ አገርም ከምንጊዜውም በላይ ተባብረው አንድነታቸውን አጠንክረው ይገኛሉ፡፡ የህወሓት ወረራ ቀጥተኛ ተጠቂ በሆኑት የአማራና አፋር ክልሎች ሕዝብ ራሳቸውን በፋኖነትና በአፋር ሚሊሺያነት በማደራጀት በራሳቸው ስንቅና ትጥቅ በአገር አድኑ ትግል ውስጥ ከፍተኛ ጀብዱ

እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ክብር ይገባቸዋል፡፡ የተፎካካሪ ፓርቲዎችም በጋራ እየመከሩ ለሕዝብና ለአገርን ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ከሕዝብ ጎን በመቆም ሃላፊነት በተሞላው መልክ ግዳጃቸውን ለመወጣት ጥረት በማድረጋቸው ሊበረታቱ ይገባቸዋል፡፡ መንግሥት ይህንን በአንድነት የቆመውን የሕዝብ ኃይል አስተባብሮና አቀናጅቶ በሰላምና በሕግ መተዳደርን እምቢ ያለውን አሸባሪውና አጥፊውን የህወሓት ኃይል ከትግራይ ሕዝብ ነጥሎ ዳግም እንዳይነሳ አድርጎ በመምታት ጦርነቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅና በትግራይም ሆነ በመላ ሀገራችን ሰላምን ማስፈን አለበት እንላለን፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ባለው ጦርነት ምክንያት ዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን መሠረታዊ ሸቀጦች መሸመት ከአቅሙ በላይ በመሆኑ ሕዝባችን በሰው ሠራሽ ችግር ምክንያት ለመኖር አለመቻሉ እጅግ በጣም አሳሳቢ ሆኗል፡፡ መንግሥት ይህን በየቀኑ እየጨመረ የመጣውን የኑሮ ውድነትና የሸቀጥ አቅርቦት በአጭር ጊዜ መቅረፍ ካልቻለ አገሪቱ ወዳልተፈለገ ችግር ውስጥ ትገባለች የሚል ሥጋት አለን፡፡

በሀገራችን ውስጥ ለ30 ዓመታት ሥር የሰደደውን መዋቅራዊና ሕገ መንግሥታዊ የጥፋት መሠረት በጣጥሶ ለመጣል መንግሥት ቁርጠኛነት ሊያሳይና ለሕዝብ ጥያቄም ምላሽ ሊሰጥ ይገባዋል፡፡ ህወሓት ከአዲስ አበባ መንበሩ የተወገደ ቢሆንም አሁንም የድርጅቱ ስግብግብ ፖሊሲ መገለጫ የሆነው የወልቃይት፣ ጠገዴና ፀለምት እንዲሁም የራያ ጥያቄ አስቸኳይ መፍትሄን ሊያገኝ ሕዝቡም እፎይ ብሎ እንዲኖር ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የነዚህ አካባቢዎች ሕዝብ ለፍትኅ በታገለ ለመሠረታዊ ልማትና አስተዳደር የሚውል በጀት ከፌደራል መንግሥቱ የሚከለከልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይገባም፡፡ መንግሥት በሰበብ አስባቡ ከእነዚህና ከሌሎችም ቁልፍ የፍትኅና የመሠረታዊ ለውጥ ጥያቄዎች የሚያሳየው ማፈግፈግና ማመንታት በአስቸኳይ ካልተገታ የሚከፈለው ዋጋ እጅግ ከባድ ይሆናል፡፡

ስለዚህ መፍትሄው ምንድነው?

በአሁኑ ወቅት መሠረታዊው ጥያቄ የአገራችን የኅልውና ጉዳይ ነው። ህወሓትና አጋሮቹ ለአገር ስጋት ከማይሆኑበት ደረጃ እስኪደርሱ ደረስ የኅልውና ጥያቄ ገንባር ቀደም ማታገያ ነው። ሕዝባዊ ትግሉም አሰላልፍና አፈረጃጀት የግድ ይህን መከተል አለበት። አገር ወዳድ ኃይል ሁሉ የትግሉ አጋርና ባለቤት ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ሕዝቡን ማደራጀትና ለላቀ ትግል ማዘጋጀት የፓርቲዎች ዋነኛ ሃላፊነት ነው እንላለን።

በሕዝብ መካከል የሚነሱ ወይም ሆን ተብለው የሚለኮሱ ቅራኔዎችን በሰከነ መንገድ ሕዝቡ ሊመለከታቸውና ሊፈታቸው ይገባል። ይህ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችም በሕዝብ መካከል ሆነው ጥያቄዎቹ ትክክለኛ ምላሽ እንዲያገኙ የመሪነት ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል።

የመንግሥት መዋቅር አሁንም ከህወሓት ናፋቂዎችና ደጋፊዎች አልጠራም። ድርጅታዊ ብቃቱ፣ የአባላቱ ጥራትና ሕዝባዊነቱ አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህም እየሰፉ የመጡትን የሕዝቡን የፖለቲክ፣ የኢኮኖሚ፣ የመሠረተ ልማትና የማኅበርዊ ጉዳይ ጥያቄዎችን ከሕዝቡ

ጋር ተቀራርቦ በመሥራት በጊዜው መፍታት ካልተቻለ የአገሪቱን ኅልውና ወደሚፈታተን ከባድ ቀውስ ልትገባ ስለምትችል መንግሥት መዋቅሩን ማጽዳት አለበት።

የአገሪቱን ኅልውና ለማስጠበቅ የሚደረጉ መቻቻሎች፣ ዓለማቀፋዊ ፖሊሲዎችና አሰላልፎች በጥልቀት እየተመረመሩ በምክንያታዊነት ሊደገፉ ወይም ሊወገዙ ይገባል። ጭፍን ስሜታዊነት ጎጅ ከመሆን አልፎ የሕዝብን አንድነትን ያላላል፣ ሕዝባዊ ኃይሉንም ይከፋፍላል። ስለዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች በግንባር ቀደምነት ትክክለኛውን አቅጣጫ ለሕዝቡ ማሳየትና ማስተማር ይገባቸዋል።

የችግሮች ሁሉ ምንጭ የሆነውን ሕገ መንግሥት ለማሻሻል መንግሥት ቁርጠኝነት ኖሮት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲሻሻል መደላድሎችን በአስቸኳይ ማዘጋጀት አለበት፡፡ መንግሥት ይህንን ሕዝቡ በተደጋጋሚ ያነሳውን ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆነ ውሎ አድሮ ሕዝባዊ መነሳሳቶች ጠንክረው የመንግሥትን ኅልውናም አጠያያቂ ደረጃ ላይ ሊያደርሱት እንደሚችሉ ከወዲሁ በመረዳት የሕዝቡ ጥያቄ መልስ ሊሰጠው ይገባል እንላለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ስለህወሓት አረመኔነት ማንም ሊነግርህ አይገባም፣ ሀገራዊ ሥልጣኑን ተቆጣጥሮ በቆየበት 27 ዓመታት የፈጸማቸውን ወንጀሎች በሚገባ ታውቃለህና፡፡ ጥፍር ሲነቀል፣ በፈላ ዘይት ሲያሰቃይ፣ አካል ሲያጎል፣ ልጅን ገድሎ እናትን በሬሳው ላይ ተቀመጭ እያለ ያሰቃይ የነበረ ጨካኝ ቡድን መሆኑን ታውቃለህ፡፡ ህወሓት ለ27 ዓመት የተመቸው ለዘራፊዎች፣ ለሙሰኞች፣ ለአገርና ለሕዝብ ግድ ለማይሰጣቸው ሆድ አደሮች እንጂ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ጥቅም እንዳላገኘ በሚገባ ታውቀዋለህ፡፡ ስለዚህ አሁን የበግ ለምድ ለብሰው የሕዝብ ተቆርቋሪ ለመምሰል የሚጥሩትን አጥፊ ኃይሎች አሳፍረህ መልሳቸው፡፡ መብትህን ለማስከበር የጀመርከውን ትግል አጠናክረህ ቀጥልበት፡፡

በውጭና በውስጥ ያሉ ጠላቶቻችን አገራችንን ለማፈራረስ እየተደረገ ያለውን የተቀነባበረውን ሤራ ለማክሸፍ በሚደረገው ትንቅንቅ ውስጥ እኛ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ዕውቀታችንን፣ ጉልበታችንንና ገንዘባችንን አስተባብረን አሁን እያደረግን ካለው አስተዋጽዖ በበለጠ ከሕዝባችን ጎን እንደምንቆም ደግመን ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

ኢሕአፓ በምሥረታው ወቅት ከሃምሳ ዓመታት በፊት ያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ማለትም፣ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነት መስፈን፣ ዳቦ ለተራበው፣ መሬት ለአራሹ....ወዘተ ጥያቄዎች ዛሬም ድረስ መልስ አላገኙም፡፡ ኢሕአፓ ለሃምሳ ዓመታት በፅናት የታገለላቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ እስኪያገኙ አሁንም ትግሉ በፅናት እንደሚቀጥል ያረጋግጣል፡፡

በመጨረሻም በህወሓት ቆስቋሽነት የተጀመረውና እየተካሄደ ያለው ጦርነት በአገርና በሕዝብ ነፃነት ላይ የመጣ በታሪካችን ታይቶ የማያውቅ አፍራሽና አጥፊ አደጋ በመሆኑ ዳር ቆመን ልንመለከተው አይገባም፡፡ ስለሆንም የወገኖቻችን ዕንባ እንዲደርቅ ዜጎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ጠንክረን በአንድነት እንታገል እንላለን፡፡

ኢትዮጵያ በልጆቿ አንድነት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኖራለች!
ድል የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!